ለሚስዮናውያን እንዴት እንጸልይ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ኤፌሶን 6: 18-20

ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤ — ኤፌሶን 6: 19

በዛሬው ምንባብ ውስጥ ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ሚስዮናውያን አንዱ የሆነው ጳውሎስ የጸሎት አጋሮች እንደሚያስፈልጉት እና ምናልባትም ብዙ እንዳልነበሩት እንመለከታለን። የዛሬው ጽሑፍ ለሚስዮናውያን እና ለሌሎች የወንጌል ሰራተኞች እንዴት መጸለይ እንዳለብን ጠቃሚ ጅምር ይሰጠናል።

እግዚአብሔር ትክክለኛዎቹን ቃላት (ተገቢ እና ውጤታማ መልእክቶች) እንዲሰጣቸው መጸለይ እንችላለን። እውነተኛውን ወንጌል (ከሐሰት ትምህርት የጸዳ) እንዲያውቁ; እና በድፍረት እንዲያውጁት (የሐሰት ሀሳቦችን እና ልምዶችን መቼ እንደሚሞግቱ እና መቼ ለመንፈስ ቅዱስ እንደሚተዉ፣ ስለ እውነት ሰዎችን እንዲሞግቱ) ልንጸልይ እንችላለን።

የሺንድለር ሊስት በተሰኘው ፊልም ኦስካር ሺንድለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ብዙ አይሁዶች ወደ ሞት (ጋዝ ክፍሎች) እንዳይሄዱ መከላከል ችሏል። በፊልሙ መገባደጃ ላይ ግን “በቂ አላደረግኩም…. የበለጠ ማዳን እችል ነበር” እያለ አለቀሰ። ሚስዮናውያን ባልደረሷቸው ሕዝቦች ጉዳይ ተመሳሳይ የጥፋተኝነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል ወይም ያልተቋጨ ሥራ እንደሰሩ ሊሰማቸው ይችላል። እግዚአብሔር ሰላምን እንዲሰጣቸው እና ያላለቀውን ስራ በእጁ እንዲተው ጠይቁ, ትክክለኛ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች እንዲመለከቱ ይመራቸዋል፤ እግዚአብሔር እንቅፋቶችን እንዲያሸንፉ ድልድዮችን እንዲያሳያቸው; ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነቶችን፣ ጓደኝነትን፣ እና ከሥራ ባልደረቦች ጋር ግንኙነቶችን እንዲሰጣቸው; እና የአገር ውስጥ መሪዎችን አገልጋዮችን እንዲያስቀጥሉ ለማሰልጠን መመሪያ እንዲያገኙ እንጸልይ።

ከሚስዮናዊያኖች ጋር እንደተገናኘን እንቆይ፣ የጸሎታቸውን እንስማ፤ ጭንቀቶቻቸውን እንቀበል እና ለእነሱ በታማኝነት እንጸልይላቸው።

ጌታ ሆይ፣ ሁሉንም የወንጌል ሰራተኞችህን በጸጋህ አጠንድታጠነክራቸውና እንድታበረታቸው እንጸልያለን። አንተን በማገልገል ደስታ ባርካቸው። አሜን።

በስታን ክሩይስ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ለመኸሩ ሠራተኞች ጸልዩ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ማቴዎስ 9:35-38

በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው። —ማቴዎስ 9:37-38

የምንኖረው የቻይና ዋነኛ ቋንቋ የሆነውን ማንዳሪንን ለመማር ቤጂንግ ነበር። ሌላ ምንም ነገር ለማድረግ ሃሳብ አልነበረንም፤ ነገር ግን በምንገኝበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው የእንግሊዝኛ ኅብረት አዲስ አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን እንድንጀምር ጠየቁን። ጀመርነው የጥናት ቡድን በፍጥነት አደገ፣ ብዙም ሳይቆይ ሰዎች በክርስቶስ ወደ ማመን ይመጡ ነበር።

አዳዲሶቹ አማኞች ጥምቀት ስርዓት ስለሚያስፈልጋቸው ለጥምቀት ዝግጅት ክፍል መራን። ከዚያም ደቀ መዛሙርት መሆን ስላለባቸው የደቀመዝሙርነት ክፍል እንዲይዛቸው አደረግን። ቤተ ክርስቲያኗ ለሌሎች ትንንሽ ቡድኖችን እንዲመሩ ሥልጠና እንድንሰጥም ጠየቁን። ሥራው ከአቅማችን በላይ እየሆነ መከመር ጀመረ። ደስተኛ ዓይነት ችግር ነበር ሆኖም ከችግርነት ሚለውጠው አልነበረም።

ለወንጌል ያለው ምላሽ ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ለመቀላቀል ዝግጁ እንደነበሩ ወይም ፍላጎት እያደረባቸው መሆናቸውን ግልጽ አድርጓል። ኢየሱስ ከ2,000 ዓመታት በፊት እንደተናገረው ግን የመከሩ ሠራተኞች በቂ አይደሉም።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ባጠቃላይ፣ ባልተደረሱ የሕዝብ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ሰዎች (ወንጌልን ለመቀበል እድሉ በሌለበት ወይም በበቂ ሁኔታ እድል በማያገኙ ጊዜ) ከሌሎች አማኝ ካልሆኑት ህዝቦች ይልቅ ወንጌል ሲሰበክ ምላሽ ይሰጣሉ። ይህንን ትልቅ ፍላጎት ለማሟላት የባህል ዘለል ተልእኮ ሰራተኞች መሰልጠን እና ማንቀሳቀስ አለብን።

እግዚአብሔር - የመከሩ ጌታ - የመከሩ ሠራተኞችን እንዲያስነሣ በታማኝነት እና በትጋት ጸልዩ።

አባት ሆይ፣ ሰዎች ልባቸውን እንዲከፍቱ ስታዘጋጅ፣ እኛን እንደ አጫጆች ልትጠቀምበት እንደምትፈልግ ለእያንዳንዳችን እንዲገባን እርዳን። አሜን።

በስታን ክሩይስ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ልዩ የግንኙነት ድልድይ መገንባት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሕዝቅኤል 4: 1-17

የብረት ምጣድም ወስደህ በአንተና በከተማይቱ መካከል ለብረት ቅጥር አድርገው፥ ፊትህንም ወደ እርስዋ አቅና፥ የተከበበችም ትሆናለች አንተም ትከብባታለህ። ይህም ለእስራኤል ቤት ምልክት ይሆናል። — ሕዝቅኤል 4: 3

አምላክ ነቢዩ ሕዝቅኤልን ሕዝቡ ታማኝ ባለመሆናቸው የሚደርስባቸውን የቅጣት ምልክቶችና የተለያዩ ትዕይንቶችን ነግሮታል። እያንዳንዱ ትዕይንት በድርጊቱ ሲፈጸም ህዝቡ ሊረዳው የሚችለውን ከንግግር ውጭ የሆነ ማሳያ አሳይቶታል አስደናቂው ተፅዕኖ ኃይለኛ ነበር.

በፊሊፒንስ ከነበረን አገልግሎት አንዱ ማሳያ ከወጣቶች ጋር በደቀመዝሙርነት ዙሪያ የሰራነው ነበር። በኔግሮስ ደሴት ላይ ያለ አንድ ቡድን ሃሌየስ ("አሣ አጥማጆች") ብሎ የሚጠራውን የወንጌል ቡድን አቋቋመ። የወንጌልን ታሪክ የሚገልጹ የፓንቶሚም አቀራረቦችን (አንዳንድ ጊዜ በቤታችን) ተለማመዱ። ከዚያም በየአካባቢው ባሉ ሰፈሮች ፓንቶሚም ያቀረቡበትን ስብሰባ ለማካሄድ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ሰሩ። ስመለከታቸው አከርካሪዬ ላይ መንቀጥቀጥ ይወጣና ይወርድ ነበር። እግዚአብሔር ቃላት ብቻውን በቂ ያልሆኑትን የሰዎችን ልብ ለመክፈት ተጠቅሞባቸዋል።

አንዳንድ የሕዝብ ክፍሎች ያልተደረሱበት ወይም ለወንጌል ምላሽ ያልሰጡበት አንዱ ምክንያት የተለመዱ ስልቶች ከእነሱ ጋር ውጤታማ ስላይደሉ ነው። እነዚያን መሰናክሎች ለማለፍ ህዝቡን እና ባህላቸውን በጥልቀት መረዳት እና ወደ ልባቸው ሊደርሱ የሚችሉ ልዩ የተግባቦች የፈጠራ ስልቶችን መፈለግ አለብን። ያ ደግሞ ቤት ከእኛ ጋር እና በዙሪያችን ከሚኖሩ ሰዎች ጋር እውነት ሊሆን ይችላል።

ጌታ ሆይ፣ አንተን ማወቅ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመድረስ ውጤታማ ስልቶችን በማዘጋጀት ምራን። ምሥራቹን በልዩ ልዩ መንገዶች እንዴት ማካፈል እንደምንችል እንድንገነዘብ እርዳን። ኣሜን።

በስታን ክሩይስ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

የተልእኳችን እንቅፋቶች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ማቴዎስ 10:5-10

ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ፥ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና። —ማቴዎስ 10:9-10

ኢየሱስ ይህን ሲል ለተልእኮ ሥራ በምንጓዝበት ጊዜ ምንም ተጨማሪ ነገር እንዳናመጣ ነበር? እነዚህ መመሪያዎች ዛሬም በእኛ ላይ ይሠራሉ? ለተልዕኮ ሥራ ስሄድ፣ አብዛኛውን ጊዜ እስከ ገደቡ ድረስ እይዛለው (አንዳንዴም የበለጠ)።

ከብዙ ዓመታት በፊት በስሪላንካ ሚስዮናዊ የነበረው ሮጀር ግሪንዌይ ቤተሰቦቹ ንብረታቸውን ከዩናይትድ ስቴትስ በ18 በርሜል እና በሁለት ትላልቅ ሳጥኖች ለመላክ እንዴት እንደሞከሩ አወራኝ፤ ነገር ግን ጭነቱ በአራት ወራት ሳይደርስ ዘግይቷል። እስከዚያው ድረስ፣ እነሱ ስሪላንካ ደረሱና ያለነዚያ ብዙ ሻንጣዎች ጥሩ ሁኔታ ሊኖሩ እንደሚችሉ አወቁ። በባሉበት ሃገር በሚገኙ ግብአቶች መገልገላቸው ከአካባቢው ሰዎች ጋር ጓደኝነትን እና ዝምድናን እንዲፈጥሩና እንዲያሳድጉ ረዳቸው።

ሻንጣቸው በመጨረሻ ሲደርስ በድንገት ጎረቤቶቻቸው የኑሮ ደረጃቸው ከእነሱ እጅግ የላቀ እንደሆነና በጣም ሀብታሞች እንደሆኑ ተመለከቷቸው። ያ ሁሉ ነገር በእነሱ እና ለማገልገል በመጡ ሰዎች መካከል እንቅፋት ፈጠረ። ግሪንዌይ በኋላ ሚስዮናውያን ንብረታቸው ለሌሎች ምን ዓይነት መልእክት እንደሚያስተላልፍ እና ሊጠነቀቁ እንዳለባቸው መምከረ ጀመረ።

ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ለብዙ መቶ ዘመናት ክርስቲያን ሚስዮናውያን ለድህነት ቃል መግባታቸው ምንም አያስደንቅም፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት ሁላችንንም ይመለከታል—የእኛ ሁኔታዎች እና አኗኗራችን ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮች ለሌሎች ምን ይነግራሉ? አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንፈልግ (ማቴ 6፡33)?

ወንጌልን በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ማድረስ ስናስብ መልእክታችን ላይ ብቻ ሳይሆን እኛነታችን እና የኛ የሆነ ሁሉ የምንሰብከው ወንጌል ላይ ምን አይነት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽኖ ሊኖረው እንደሚችል ቆም ብለን በመመልከት፤ ሚስተካከለውን በመቀየር፥ ለምንኖርበት እና ለምንደርሰው ምህበረሰብ ስብእና አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና ዝግጅት በማድረግ ሊሆን ይገባል።

አባት ሆይ ስለሰጠኸን ስጦታዎች ሁሉ አመሰግንሃለሁ። አንተን እና ሌሎችን ለማገልገል እንቅፋት የሚሆንብን የትኛውም ነገረ በልግስና እንድናጋራ፤ ወንጌልን የሚሸፍን የትኛውም የሕይወት ልምምድ፥ የኑሮ ደረጃን ስላንተ ስንልን እንድንቀይር እርዳን። ኣሜን።

በስታን ክሩይስ የተጻፈ ከ[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/) ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — የሐዋርያት ሥራ 8:4-8

የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ። — የሐዋርያት ሥራ 8:4

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብታችሁ “ይህ ለምን ሆነ?” ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ።

ጆኒ እኔ አብሬው የምሠራው ሚስዮናዊ ሲሆን በሄይቲ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ያገለገለ ነው። በፖለቲካ ትግል እና በበዛ ብጥብጥ ምክንያት ከቤተሰቡ ጋር ወደ አሜሪካ ተመለሰ። አስቸጋሪ ሽግግር ነበር፤ በጣም የሚወዳቸውን ባልደረቦች እና ጓደኞች እንዴት ትቶ ይሄዳል? በእንደዚህ ዓይነት ያልተረጋጋ አካባቢ ውስጥ የመኖርን አሰቃቂ ሁኔታ እንዴት ያስተናግዳሉ?

God did something like that with the early Christians too—like Philip, who was forced to flee to Samaria. In all kinds of situations the Holy Spirit continues to spread the good news of Jesus in surprising ways around the world.

*Dear God, even when we are recovering from a painful situation or heartache, you pour out your healing in your good time and provide new opportunities for us to serve you. Thank you, Lord! Amen.*

ነገር ግን ጆኒ እና ሚስቱ መረጋጋት እና ከነበሩበት ውስጣዊ ጭንቀት መላቀቅ ሲጀምሩ አንድ አስደናቂ ነገር አገኙ። በሺህ የሚቆጠሩ የሄይቲ ሰዎች እሱ እና ቤተሰቡ አሁን ወደሚኖሩበት ቦታ ተዛውረው ነበር፣ እግዚአብሔር የሄይቲን ማህበረሰብ ባሉበት ቦታ ወይም በገዛ ከተማቸው እንዲያገለግሉ እድሎችን ፈጠረላቸው።

ስለዚህ አሁን ጆኒ የሄይቲ መሪዎችን ለማሳደግ እና የሄይቲ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ከሄይቲ መጋቢዎች ጋር መስራት ጀመረ። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ 10 አዳዲስ የሄይቲ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ህልም አላቸው! እግዚአብሔር አሳዛኝ ሁኔታን ወስዶ በሰሜን አሜሪካ አዳዲስ እድሎችን ለመክፈት ተጠቅሞበታል!

አምላክ ከጥንቶቹ ክርስቲያኖችም ጋር ተመሳሳይ ነገር አድርጓል፤ ልክ እንደ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ለመሰደድ ተገደደ። መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች የኢየሱስን ምሥራች በሚያስደንቅ ሁኔታ በዓለም ዙሪያ ማሰራጨቱን ቀጥሏል።

የገባችሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ ምን ይሆን፣ ከስራ መባረር፣ የመኖሪያ ስፍራና መስራቤት መቀየር ወይስ ህብረት ከምታደርጉበት ቤተክርስቲያን በአንድም በሌላም ምክኒያት ለመቀየር መገደድ፤ እግዚአብሔር ይህን ለምን ያደረገ ይመስላቹሓል። አስገዳጅ ሁኔታዎቻችሁን መቀየተር ስላማይችል ወይም እናንተ በምቾቶቻችሁ እንዳትኖሩ በፍጹም ለእናተ የሚያስባትን ሀሳብ እርሱ ያውቃል። ነሆናችሁት የሕይወት አጋጣሚ እና መስመር ሁሉ እግዚአብሔር እናንተን የሚሰራበት እና በእናነተ በኩል የሚሰራበት አላማ አለው ስለሆነም፤ ትልቁ ጥያቄያችሁ መሆን ያለበት ፈቃድህን ብቻ ግለጥልኝ አሜን ይሁን ማለት መሆን አለበት፤ በጸሎት በፊቱ የመጣብኝን ለውጥ ለወንጌልህ፣ ለሰዎች መዳን፣ በሕይወቴ አላማክን ለመፈጸም ተጠቀምበት በሉት/

አባት ሆይ፣ የሕይወቴ አጋጣሚዎች ሁሉ በአንገተ ቁጥጥር ውስጥ ናቸው፤ ለምን እንደሆኑ የሚገቡኝም ሆኑ ማይገቡኝ ሁሉ ለአላማክ እንድትጠቀምበት እለምንካለው! ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

የተደበቁት አማኞች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — 1 ነገሥት 19: 9-18

እኔም ከእስራኤል ጕልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፥ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፥ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ… 1 ነገሥት 19:18

ኤልያስ ድካም ውስጥ ገብቶ ነበር'፤ የበኣልን ነብያት ገጥሞ ታላቅ ድል ካደረገ በኋላ፣ አሳዛኙ የአክዓብ መንግስት እንደሚናወጥ እና እንደሚወድቅ አስቦ ነበር፤ እንደዚያ አልሆነም። ይልቁንም ነፍሱን ለማዳን መሯሯጥ ነበረበት። ( 1 ነገሥት 18:16-19:9 ተመልከት።) ኤልያስ ወደ ኮሬብ ተራራ (ሲና) ሸሸ፤ በዚያም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ "እኔ ብቻዬን ቀረው" ብሎ ጮኸ።

እውነት? እግዚአብሔርም ሒሳቡን እንዲያሰላ እረዳው። እግዚአብሔር በእስራኤል ውስጥ ለበኣል ያልተሰገዱ ሰባት ሺህ ሰዎች ነበሩት።

የእኛ ቅርብ ተመልካችነት ዛሬ በዓለም ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ሥራ አርቀን ለማየት እንቅፋት ይሆንብናል። ለምሳሌ በመካከለኛው ምስራቅ ከ12 ሚሊዮን በላይ ክርስቲያኖች እንዳሉ ታውቃላችሁ? በየጥቂት አመታት፣ ከሁሉም መካከለኛው ምስራቅ ካሉ ክርስቲያኖች ጋር ለህብረት እና ለአገልግሎት እቅድ ከሚያዘጋጁ ክርስቲያኖች ጋር የመገናኘት እድል አለኝ። ሁሌም "በዓለም ዙሪያ ባሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ተረስተናል" ይሉኛል። ለእነርሱ ከገባኋቸው ቃል ውስጥ አንዱ የእምነት ባልንጀሮቻችን እንዳሉ እንዲያውቁ እና እነርሱን ወክለው እንዲጸልዩ ማበረታታት ነው።

ክርስትና በተወለደበት የዓለም ክፍል ምሥክሮችን ለማበረታታት የጸሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ሀብታችንን ማሰባሰብ የምንችለው እንዴት ነው? በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን አስታውሱ!

*ጌታ ሆይ የማናያቸውን ሰዎች ችላ የማለት ችግሮቻችንን ይቅር በለን። በቤተክርስቲያን የለባቸውም ብለን ከምናስባቸው አገሮች ካሉ ክርስቲያኖች ጋር በመንፈስህ አንድ አድርገን። ኣሜን።*

በቦብ ኽርስፒንክ የተጻፈ ከ**[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/)** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ